# በመለስ ዜናዊ ታላቅነት መጠራጠር ምኑ ላይ ነው!?

“የመለስ ታላቅነት ምኑ ላይ ነው” በሚል ርእስ ከባድ የስህተት መናፍስት ተፅፏል- “ሎሚ” በተሰኘች መፅሔት በመጋቢት 2005 ዓ/ም እትሟ ሙግት በተባለ ዓምድ ገፅ 25 ላይ። ስለ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ እንኳን በውሸት በእውነት መፃፍም መናገርም ይከብዳል። ለምን ስለወርቃማው ገድላቸው በትክክል ለመግለፅ የመረጃው ምንጭ ሊገኝም ላይገኝም ከመቻሉም በላይ ምንጩ ቢገኝ እንኳ የየግል አስተያየት ከመግለፅ ባለፈ የልካቸውን ያህል ማስቀመጥ የራሳቸው የመለስን ያህል አቅም የሚጠይቅ ይመስለኛል። ይህን ፅሑፍ እንዳቀርበ መነሻ የሆነኝ የመፅሂቷ መናፍስት ግን በድፍረት ‘አዋቂ ኩሉ’ በመሆን ዓለም የመሰከረለትና እየመሰከረለትም ያለውን የመለስ ታላቅነት በድፍረት ለማብጠልጠል መሞከር ተገቢ ስላልሆነ ሂወታቸውን ሙሉ ለዚች ድሃ አገር ለለገሱ ታላቅ የእጃቸውን እንንገርላቸው ለማለት ነው። ወይ አድርግላቸው ወይ ንገርላቸው ነውና።

በርግጥ ከጠላቻ በመነሳት ያመጣልህን መቀባጠር የዲሞክራሲን ምህዳር አንዱ ጎኑ ነው ይባል ይሆናል። አዲስ ውሸትና አዲስ የጥላቻ መግላጫም ሆኖ አይደለም። ነገር ግን ከኢትዮጵያውያን ባህልና ልምድ ውጪ ለምን ይዋሻል? ለምንስ የሚታየውን የሚዳደሰውንና የሚጨበጠውን የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊን ታላቅነት ለመካድ ይሞከራል? “ማን ላይ ሁነሽ ማንን ታሚያለሽ” እንዲሉ ሆነና በፓረቲያቸው ኢህአዲግ ጠንካራ አስተዋፅኦ በተፈጠረው በነፃነት የመፃፍና የመናገር መብት ተጠቅመው ታላቅነታቸውን ለማሳጣት መዳዳት “እንደተለመደው ነው” ተብሎ መታለፍ ስለሌለበት በግሌ በመለስ ዜናዊ ታላቅነት መጠራጠር ምንኑ ነው በማላት ታላቁን መሪ መለስ ዜናዊን ባይመጥንም ለኔ የሚመጥን ሓሳብ ለማቅረብ ነው።

ደግሞም እኮ ውሸቶች ሲደጋገሙና ግዜ በወሰዱ መጠንና ሳይጋለጡ ሲቀሩ እውነቱን እንዲጨብጥ ያልተደረገ ትውልድ እውነት ለሚስለው ይችላል። ሓቁን ለትውልድ ማስተላለፍም ታሪካዊ ሓላፊነት አለብን። ምክንያቱም ትክክለኛ መረጃ ለትውልድ ሳይተላለፍ ሲቀር ታሪክ ይዛባል እየተዛባ እንደመጣው። “የባብዬን ለማምየዬ ወይም የማምዬን ለባብዬ” እየሆነ ወርቃማ ታሪክ ሲዳፈን ወይም ላልሰራው ሲሰጥ እንደቆየዉ ሁሉ መረጃ የማስተላለፍ ጉድለት አሁንም ለወደፊትም እንዲቀጥል መፍቀድ የለብንም።

ስላለፈው የኢትዮያ ህዝብ ታሪክ በተሟላ ሁኔታ የተፃፈና የተቀረፀ መረጃ ስለሌለ ፀሓፊዎች እንደየፍላጎታቸውና በግምት ታሪክን ሲያጣምሙ፣ ሲያወላግዱና ጭራሽ ሲያዛቡ የኖሩት አይበቃም ወይ!? ከቅርቡ ብንጀምር . . . ስለ አገር አንድነት ተቆረቆሪውና ሽጉጣቸውን በመጠጣት ጀግንነትን ስላስተማሩት ስለ አፄ ቴዎድሮስና ጀግኖቻቸው እነ ገብርየ የተባለው በጣም ጥቂት ከመሆኑም በላይ እንደሌሎቹ የሚታወስበት ሓወልት ተነፍጎዋቸው ቆይቷል። ስለዚህ ጉዳይ ለወደፊቱ ይነገር ይሆናል ይገባልም።
. . . ስለ አገር ስለተቆርቆሪውና የአገር ድንበር ቀይ ባህር ድረስ በማስከበር ግንባራቸውን ለባዕድ ወራሪ ጥይት በመስጠት መስዋእት ሆኖው ትውልድን ስለአስተማሩት አፄ ዮውሃንስና ጀግኖቻቸው የራሶች ራስ የአፍሪከ ጀኔራል አሉላ አባነጋ የተነገረው እጅግ በጣም ትንሽ ከመሆኑም በላይ የተዛቡ ፣ ለሌሎች የተሰጡ ወርቃማ ታሪኮች እንዳሉ

ሆኖው እንደሌሎቹ የሚታወሱበት እና ላበረከቱት አገር የማስከበር አስተዋፅኦ የሚያንፀባርቅ ሓወልት ተነፍጎዋቸው ቆይተዋል። ስለዚህ ጉዳይ ለወደፊት ይነገር ይሆናል ይገባልም።

. . . ዓድዋ ላይ ወራሪን ድል ያደረገውን የኢትዮጵያን ጀግና ስለመሩትና መረብ ምላሽ አገር ቆርሰው የጣልያን ግዛት እንዲሆን ስለፈረሙት አፄ ምኒሊክና ጀግኖቻቸው በተሻለ ተነግሯል እንኳንም ተነገረ። የሚታወሱበት ዘናጭ ሓወልት ታንፆላችዋል እንኳንም ታነፀላቸው። ነገር ግን ያልተነገሩ ታሪኮች ስላልዋቸው ለወደፊቱ ይነገር ይሆናል - ይገባልም።

ኢትዮጵያንና ህዝቧን ለወራሪው የኢጣሊ ጦር አስረክበው በመፈርጠጥ እንግሊዝ-ለንደን ውስጥ ስለመሸጉት አፄ ኃ/ሥላሴና ተከታዮቻቸው የተባለም በቂ አይደለም። ለወደፊት ይነገር ይሆናል - ይገባልም።

. . . "አንድ ሰውና አንድ ጠብመንጃ ብቻ እስከንቀር ድረስ በቆራጥነት እንዋጋለን" እያሉ ሲፎከሩና ሲያስፎክሩ ፣ ሲደሰኩሩና ሲያስደሰኩሩ ከርመው የኢትዮጵያን ሃብት አሟጠው በመዝረፍ ወደ ዙንቧቤ ስለ ፈረጠጡት "ቆራጡ" መሪ ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማርያምና ተከታዮቻቸው ደርጎቹም አልተነገረም ለወደፊቱ ይነገር ይሆናል- ይገባልም።

. . . ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከጥቂት ዓመታተ በኋላ በኢኮኖሚ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ጎራ ለማሰለፍ በህዳሴው ጎዳና እየመሩ ላፍታ ሳያረፉ ስላረፉ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊና ጀግኖቻቸውም አልተነገረም ብቻ ሳይሆን አለፎ አልፎ እየተዛባ እየተበረዘና እየተካደ ስለሆነ ተስተካክሎ መነገር አለበት። ይኸውና እየተናገርን ነው።

እናም ታላቁ መለስ ዜናዊ በተላላቆች እየተመሩና ተላላቆቹን እየመሩ ስለአከናወኑዋቸው ገድለ ታሪካቸው ታላቅነታቸውን ስለሚመሰክሩ የተወሰኑት እንደሚከተለው ብጠቅስ፣

"የመለስ ታላቅነት ምኑ ላይ ነው" ብለው ለደፈሩት ፀሓፊ የተዛባው ሀሳባቸውን በተስተካከለ መረጃ ይቀይሩ ዘንድ ይረዳል ብየ አምናለሁ። ደግሞም 'ኮ ስለ መለስ መናገር ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ትግልና ድል መናገር ማለት ነው። ስለ መለስ መናገር ስለትግላቸው መስመር መናገር ነው። ስለዚህ መለስ ብለን በመንናገርበተ ግዜ የትግሉ መስመር ማለት እንደሆነ ልብ ይለዋል።

ለነገሩ ታላቁ መለስ ስለ ታላቅነታቸው እንዲነገር አይፈልጉም ነበር ብቻ ሳይሆን በግላቸው ታላቅ የመሆን ዓላማ እንዳልነበራቸው ደጋግመው ይናገሩ ነበር።

እንግዲህ ታላቅ ማለት በእንግሊዝኛ ቃሉ Great ብለን ካልነው ትርጉሙ Admired — extremely Good in Ability or Quality and therefore Admired by many people. በስራው ችሎታና ጥራት በህዝብ አድናቆት የተቸረው ሰው እንደ ማለት እንውሰደውና ይህ መግለጫ ከታላቁ መለስ ዜናዊ በእጅጉ የሚስማማ ነው።

1. የሎሚ መፅሒት ፀሓፊ "ታላቁ እስክንድርን በጦርነቱና ማንዴላን በአቋመ ብርትነቱ ታላላቆች ያሰኛቸዋል" ብለው በጠቀሱት መሰረት እንኳ ብንሄድ እነዚህ ቁም ነገሮች ታላቁ መለስ ዜናዊም ታላቅ ከሚያሰኙ መግለጫዋች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ጦርነት ታላቅ የሚያሰኝ ከሆነ በእኔ እምነት ፍትሓዊ ጦርነት ብየ በመውሰድ መለስ በረጅሙ ጦርነት ያውም የርስ በርስ ከባድ ጦርነት ገብተወ ተመሪም መሪም ሆኖው ብዙ

ግዜ የጦርነቱ ማሃንዲስ በመሆን ለድል የበቁ፤ ከአቋመ ብርቱነት አንፃር ሲለኩ ደግሞ ያለ ማጋነን የመለስ ብልጫ አለው። መለስ በአንደኝነት የሚጠየፉት በአቋም አለመፅናትን ነው። አቋም ሲይዙ በጥልቅት አጥንተው ከአገርና ህዝብ ጥቅም አኳያ ያለውን ፋይዳ መዝነው በፅናት ያራምዱታል። ከራሳቸው በያዙት አቋም ይፀናሉ ይበረታሉ ብቻ ሳይሆን ሌላውን በማሳመን ያላቸው ብርታት ለማን ይነገራል። ስለዚህ መለስ የጦርነት አቀንቃኝ ባይሆኑም ጦርነትን በጦርነት በማርገብ ወደ ሰላምና ልማት ከመለወጥ አኳያ በአማራራቸው ስር ያለው የኢትዮጵያ ህዝባዊ ሰራዊት አገሩን ከማስከበር አልፎ በሶማልያው ህንድ ውቅያኖስ ድረስ ፣ በላይበርያው ፓስፊክ ውቅያኖስ ድረስ በተባበሩት መንግስታት ዘምቶ ቁጥር አንድ የአፍሪካ ውጤታማ ሰራዊት ሆኗል።ይህ እንግዲህ የመለስ ዜናዊን ታላቅነት አንዱ መገለጫ ነው።

2. ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የአገር ሰላም አንድነትና እድገት የሚረጋገጥበት መንገድ በመቀየስ ላይ የጎላ አስተዋፅኦ ነበራቸው መለስ ወጣት ሆኖው ትግሉን ለመቀላቀል ሲወስኑ፣ በረሃ ወጥተው ከተራ ታጋይ እስከ አመራር ሆኖው ሲታገሉና ስያታግሉ በኢትዮጵያ ተቀጣጥለው የነበሩት ግጭቶች ተወግደው ሰላም፣ አንድነትና እድገት በምን መልኩ መረጋገጥ እንደሚችል ከጓዶቻቸው ጋር በመሆን ብሩህ የሆነ የትግል መስመር ነድፈው፣ይኸውና አገራችን በአመራራቸው ወደ ተሻለ እድገት እያመራች ነው። ይህ አገርን ከጦርነት አላቆ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ሲንገዳገድ የነበረውን አንድነታችንን አጠናክሮ አገሪቱን ወደ ጥንታዊው ታላቅነትዋ የመመለስ ተስፋን የሚያሰንቅ ቀያሽነታቸው ታላቅነታቸውን ያስመሰክራል።

3. ታላቁ መለስ ዜናዊ የቀየሱት የትግል መስመር አገር ውስጥ ብቻ የሚታጠር አይደለም። አለምን በዚህ መዋእል እያስጨነቃት ስላለው የኢኮኖሚ /የገበያ ቀውስ ለመፍታት የግል ሴክተሮችና የመንግስታት ሚና ምን መሆን እንዳለበት በግልፅ ያቀረቡና እየተከራከሩም ቆይተዋል። በተለይም በበለፀጉ አገሮች የጋጠመውን ቀውስ በመለስ መንገድ ለመፍታት ቢሞከር ኖሮ ዓለም ከብዙ የኢኮኖሚ ታግዳሮቶች ትተርፍ እንደ ነበር የመለስ አድናቂ የሆኑት የኮሎምቢያው ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር በየአጋጣሚው ሲያወሱት እንሰማለን። ታዲያ የዓለም አገሮች እንደየ እድገት ደረጃቸውና ነባራዊ ሁኔታቸው ጋር የሚጣጣሙ የኢኮኖሚ/ገበያ መንገዶች ተንትኖ ከማስረዳትና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ አቅርቦ የዓለም ህዝቦች ከሚጎዱባቸው ቀውሶች ለመገላገል በጎ አስተዋፅኦ ከማበርከት በላይ ታላቅነት ምን ይሆን!?

4. ስለ ዓለማዊ (Global) የአየር መዛባት መንሲኤዎች፣ እያስከተለው ስላለው ችግርና መፍትሔዎቻቸው መተንተን ፣ መከራከር ማሳመንና አፍሪካን ወክለው ያስመዘገቡት ፋይዳና ያገኙት ዓለም አቀፋዊ አድናቆትስ የመለስ ዜናዊን ሌላው የታላቅነታቸው ገፅታ አይደለም ወይ!? ባለብዙ ፋብሪካዎች የበለፀጉት አገሮች የሚረጩት ካርቦን ዓለምና ህዝቧ ንፁህ አየር ተነፍጎዋቸው አየር ተዛብቶ የተለያዩ አደጋዎች ስለመውረዳቸው አስረድተው ስለዚህም የተበደለችው አፍሪካ መካስ እንዳለባት የሞገቱና የረቱ/ያሳመኑ ብልህና ምርጥ መሪ ነበሩ . . . እናም ታላቅ!

5. መለስ ዜናዊ በሳይንሳዊ ክርክራቸውም ታላቅ ነበሩ። ክርክር ሲባል በበቂ እውቀት ላይ ተመስርተው ሃቅን ሃቅ ላይ እየገነቡ በተፃራሪ የሚከራከረውን ሀይል በሚያሳምን ወይም መፈናፈኛ በሚያሳጣ መልኩ የማቅረብ ችሎታቸው በእጅጉ የላቀ ነበር። ተከራካሪው ለመቀበል ባይፈልግም ለሦስተኛ አካል /Audience/ ትእዝብት ውስጥ በሚጥል አኳኋን ስለሚያቀርቡት የማሳመን/የመርታት አቅማቸው ከፍተኛ ነበር። ለምሳሌ፡ በአገረ ቶጎ-ሎሜ ከተማ ውስጥ በተቀመጠው የአፍሪካ ሃገራት መሪዎች ስብሰባ የአፍሪካ ሕብረት ፅሕፈት ቤት ከአዲስ አበባችን እንዲነሳ በተሞከረበት ሽረባ ታላቁ መሪያችን እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው

ብቻ ሳይሆን አሳማኝና የማያፈናፍን እውነታን በመተራስ ያቀረቡት ሀሳብና ክርክር እናም ያስመዘገቡት ድል የኢትዮጵያ ህዝብ በእጅጉ ኮርቶባቸዋል። አድናቆቱም ቸሮዋቸዋል። የዚህን ክርክር ሙሉ ቃል የንግሊዝኛ ቃሉ እስከ አማርኛ ትርጉሙ በጋዜጠኛ አለሜ ቡቃያ ነሐሴ 2004 ዓ/ም በተፃፈ "ከመለስ አንደበት" በተሰኘ መፅሓፍ ገፅ 22-25 በመመልከት በታላቁ መሪያችን መለስ ዜናዊ በሳል ሀሳብ መኩራት ይቻላል። እናም ታላቅነት ካሉ መሪዎች አንፃር ሊመዘንም ስለሚገባ መለስ ይህን ክርክር ካቀረቡ በኃላ ቀጥሎ የተከራከረም ይሁን በግልፅ የተቃወመ መሪ አልታየም። መፈናፈኛ አላገኘማ! እናም የኢትዮጵያ ታላቅነት የተፈታተኑቱም ጥቂት መሪዎች በአለም መድረክ አጋልጠው ውድቅ በማድረግ "ከሸረባ ውጪ እውነታዎች ይቅረቡና እንከራከረበት" ብለው ሲጋብዙ አንድም ያገር መሪ ትንፍሽ ሳይል መቅረቱ ብልጫቸውን ያሳየ መገለጫ ነበር። እናም መለስ ለኢትዮጵያ /ለአፍሪካ ምኗ ነበሩ. . . ታላቅ! ''

6. እኒህ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ያልታሰበና ያልታየ መፍትሄና ኣቅጣጫው በማሳየትና በመምራት ተወዳዳሪ ስላልነበራቸው ታላቅነታቸው የሚያስረግጥ ሌላው ፈርጅ ነው። ለምሳሌ የኛ የኢትዮጵያዊያን ዋነኛው ጠላት ድህነት ስለመሆኑና የሁሉም ችግሮቻችን ማጠንጠኛ ድህነታችን ስለሆነ እናም ካስወገድነው መሰረታዊ መፍትሄ እንደሆነ ኣስረግጠው በመምራታቸው አገራችን አሁን የዓለም ቀልብ ስባለች ።ህዝቡ ከጠባቂነት እየተላቀቀ በራሱ ጥረት ብቻ እንደሚያልፍለት ኣምኖ ባደረገውና እያደረገው ባለው ርብርብ ብዙዎች ምሊዬነሮች ሆኖዋል። ለብዙዎች ተሞክሮ መቅሰሚያ ለመሆን ታድለዋል። ስለዚህም ከሩቅም ከቅርብም አገሮችና ብዱኖች በጥርጣሪ እየተያዩ " ታሪካዊ ጠላቶቻችን" እየተባባልን ከመናቆር ተላቀን ዋናው ጠላቶችን የጉያችን አስቀያሚው ድህነታችን መሆኑን እንዲረዳንና እንድናጠፋው የተነተኑ፣ ያስረዱ፣ ያሳመኑ፣ ያሰለፉና አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ እናም ብዙሀኑን የጠቀሙ መሪ መለስ ናቸው። ታላቁ መለስ ዜናዊ . . . ታላቅነት ብዙሀኑን በዘላቂነት መጥቀም ቀዳሚው መመዘኛ እስከ ሆነ ድረስ!

7. በተሟላ ስነ ምግባርና ሁሉን አቀፍ ጥልቅና ሰፊ እውቀት የተካኑት መለስ በኢትዮጵያ ታስቦ፣ ተሰምቶም ተሞኩሮም የማይታወቀውን "ከስልጣን ወርደን ለሌሎች እናስረክብ" ማለታቸውስ . . . ለስልጣን ርክክቡ በግዜ የታጠረ መመሪያ አውጥተው "ከስልጣን መውረድ እኔ ልጀምረው ብለው መከራከራቸውስ. . . ለሚያፈቅሯትና መስዋእት ለከፈሉላት አገራቸው ሰላም ፣ መተማመንና መተቃቀፍ ለጠንካራ አንድነት - ለጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ብቃትና ራስዋን የቻለች አገር ለመፈጠር አይደለም ወይ? ይህ በኢትዮጵያ ፈፅሞ ታይቶ የማይታወቀው በሰላም ስልጣን የመረካከብ ተግባር ለአገራችን ፋይዳው ጥልቅ ስለሆነ አድርገውታል. . . መመርያው ከህልፈታቸው በኋላም በጓዶቻቸውና በጓደኞቻቸው ደግሞም በህዝባቸው እየተተገበረ ይገኛል- ይቀጥላልም- ቅን ለምናስብ ከዚህ በላይ የታላቅነት መገለጫ ያለ አይመስለኝም።

8. ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የሚያሳምን ሀሳብ ካገኙ ሳያቅማሙ ይቀበሉታል ብቻ ሳይሆን አድነቀውና አወድሰው ያዳብሩታል። መመሪያቸው አድርገውም ያስተገብሩታል. . . "እኔ ያነበብኩ የተመራመረኩና መሪ በመሆኔ የኔን ብቻ ተቀበሉ" ማለት ፈፅመው ኣያስብቱም አይወጣቸውም። የማይቀበሉት ከሆነ የማይቀበሉበት ምክንያታቸውን ገልፀው ሆኖም የብዙሀኑ አቋም ከሆነ በብዙሀኑ ድምፅ ተገዝተው ላላመኑበት አቋም በፅናት ይፈፅሙ እንደ ነበረ በብዙ ምሳሌዎች ማረጋገጥ ይቻላል። ምን እንኳ ይህ ዲሞክራሲያዊ ልምድ የታጋዩ ድርጅታቸውና ህዝባቸው ባህል ቢሆንም የሚመራው በሳቸው እስከ ሆነ ድረስ የመሪ ሚዛን መውሰዳቸው ስለማይቀር ሀሳብን በሰላምና በነፃ ማሸራሸር፣ መቀበልና አለመቀበል የኢትዮጵያውን ልምድ እንዲሆን መደረጉ ምክርቤቶቻችን አብነቶች ናቸው . . . በብዝሃኑ መግዛት

ለቀረርቶ አይዳርግም፣ ጦር አያማዝዝም፣ አያቀያይምም. . . እናም አብሮ ተባብሮ የመኖር ተስፋችን ያለመለመ ነው . . . እናም በዚህ ጉዳይ ላይ የመለስ ጥረት ጫን ያለ ስለሆነ ታላቅነታቸውን ነው የሚያረጋግጥልን።

9. ብዙሃኑን ቅድሚያ ለመጥቀም መስራትና መጥቀም ታላቅነትን ያረጋግጣል። በተለይም ደግሞ በአገር መሪነት ደረጃ ህዝብ የሚጠቀምበት መሰረት መጣል ታላቅ ያስብላል። እናም መለስ በአንባቢነታቸው፣ በአረዳዳቸው ፣ በፀሀፊነታቸው፣ በተንታኝነታቸው፣ ፍፃሜዎች ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘባቸውና ወደ ጥቅም በመለወጣቸው፣ በቋንቋ ችሎታቸው. . . ለዚህ ሁሉ በፍጥነት ማከናወናቸው ተወዳዳሪ አለማግኘታቸው . . . በሁሉም አቀፍ /All sided Personality ታላቅ ናቸው። ለዚህ ታላቅነታቸው ብዙ ማስረጃዎች መቆለል ቢቻልም የአገሮች መሪዎችና እውቅ የአለማችን ሰዎች ስለመለስ ታላቅነት የተናገሩትን ማየት በቂ ነው። ለምሳሌ የተባበሩት አሜሪካ ፕረዚደንት የነበሩት ቢልክሊንተን "እኔ ከምናገር መለስ ሲናገሩ መስማት እመርጣለሁ" ብለዋል። BBC ስለ መለስ ሲናገር አልፎ አልፎ በታዳለ መዋእል ከሚፈጠሩት ልዩ ችሎታ ካላቸው ሰዎች አንዱ እንደነበሩ አብራርቷል። ለዚህም ነው የአገር መሪዎች ፣ የአለም ሚዲያዎች አፋቸውን ሞልተው መረጃዎቻቸውን ደርድረው "Meles a great leader" ሲሉ ያወደስዋቸውን ታላቁን መለስ "ታላቅነታቸው ምኑ ላይ ነው" ብሎ መሞነት ታላቅ ድፍረት ነው ያልኩት። እንግዲህ የሎሚ መፅሔት ፀሓፊ ሆይ እውን የመለስ ታላቅነት የማያሳይ ትራኮማ ይዞዎት ከሆነ ቢልክሊንተንን ፣ ባራክ ኦባማን፣ ጀንዳይ ፍሬዘርን፣ ሱዛን ራይዝን፣ ደቪድ ካሚሮንን፣ ቶኒ ብለየርን፣ አንጀላ መርከል ፣ ታቦ እምቤኪን፣ኤለን ጆንሰንን፣ ዑሞር አልበሽርን፣ ኦባ ሳንጆን BBCን ወ.ዘ.ተ ይጠይቁ ወይም ያሉትን ይመልከቱ። . . . ወደአገር እንመለስ።

10. ከመለስ ታላቅነት መገለጫ አንዱና ኢትዮጵያውያንን በምልአት አስደስቷዋልም አሰባስበዋልም በሚያስብል መልኩ የፈፀሙት "ፕሮጀክት x" ን ነው። የታላቁን የህዳሴ ግድባችን ሀሳብ ከማመንጨት አልፎ ፣ ታቅዶ የግድቡ ስራ ለአንድ ደቂቃም ላይቆም መጀመሩ . . . መቀጠሉስ በአቋማቸው የፀኑ፣ በራሳቸውና በህዝባቸው የሚተማመኑ የታላቅም ታላቅ ናቸው። መለስ ዜናዊ ያለሰብነውን ያልገመትነውን ምናልባትም አንዳንዶቻችን ያልተመኘነውን እንደህልም ወይም ቅዠት የሆና ዜና አብስረውናል ይህ ከታላቆች የሚለገስ ፀጋ ነው።

እናም ስለ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በዙ ማለት ቢቻልም ተያያዥነት ያላቸው ጥቂት ነጥቦች የፃፍኩት ስንቃወምም፣ ስናወላግድም፣ ስናጣምምም፣ ስንዳፈርም ልክ እንዲኖረው፤ ያለፈው በቅቶ የአሁኑ ትውልድ በምክንያት ለመደገፍና ለመቃወም መረጃ ላይ ተንተርሶ የሚሄድ ነውና ይህን ያህል መዳፈሩ አያግባባም ለማለት ነው። በተረፈ እንነጋገርበት።

የታላቁን መለስ ፈለግ ተከትለን የኢትዮጵያን ህዳሴ እናበስራለን!!

**አብርሃ ገ/አረጋዊ - መቐለ**

abrha66@gmail.com